# በዲሞክራሲያዊነት ዳባ የሽብርተኛነት ዳባ

**ከፀጋዬ ደባልቀው**
**ዋሺንግተን ዲሲ**

ውድ ሃገራችን ኢትዮጵያ ለዘመናት ቀፍድዶ ጠፍሯት ከቆየው ከኋላቀርነትና ከድንቁርና ከበሽታና ባጠቃላይ ለዘመናት ተከናንባው የዘለቀችውን ድቅድቅ የጨለማ ማቅ ከትከሻዋ አሽቀንጥራ በመጣል በብሩህ የተስፋና የተጨባጭ ፍሬ ሃዲድ ላይ ከተፈናጠጠች ይኸውና ጥቂት ዓመታትን አስቆጥራለች፡፡

ድህነት ያለፉት ትውልዶች የተረት ተረት መዝሙር አልበም ሆኖ እንዲዘከር ሁነኛ መቀመጫ በሆነው በታሪክ ሙዝየም የማኖሩ የአሁኑ ትውልድ የማያባራ ቁርጠኛ ተጋድሎ ግን የአልጋ በአልጋ ጉዞ እንዳልሆነ ቢታወቅም በየትግል ምዕራፉ ብቅ ጥልቅ እያሉ የሕዝቡን የዲሞክራሲ የሰላምና የልማት ሶምሶማ ፈር ለማጨናገፍ ጥቂቶች የሚያደርጉት የመቃብር አፋፍ የቀቢጽ ተስፋ መፍጨርጨር የኋላ ኋላ መሪር የሽንፈት ፅዋቸውን የመጋታቸው እውነታ ግን አይቀሬ እየሆነ ቀጥሏል፡፡

ሰሞኑን ደግሞ የኒውዮርክ ከተማ ሰማይ ጠቀስ ፎቆችን በምሽግነት የሙጥኝ በማለት በመፏለል ላይና በሎንዶን ጥንታዊ ጎዳናዎች እየተንጎራደደ ያዙኝ ልቀቁኝ በማለት በጋራ በማጓራት ላይ ያሉት ዘመናዊያኑ የግንቦት 7 ንቅናቄ መሪዎች የሚያወርዱት ሙሾ በዓይነቱ ልዩ የሚያሰኘውን የቅጥፈትና የብለጣብልጥነት አባዜ ይዞ ብቅ ማለቱ ለጉድ የሚያሰኝ ነው፡፡

የድል አጥቢያ አርበኛነት መታወቂያና የምስክር ወረቀት በ500 ዶላር እየተቸበቸበ በድል ማግስት በአዲስ አበባው የመስቀል አደባባይ ለምስክርነት ይዛችሁት ብቅ የምትሉት ወርቃማ የጀግንነት ማስረጃ ነው በማለት በውጭ አገር ላባቸውን አንጠፍጥፈው አበሳቸውን አይተው ያጠራቀሟትን ቤሳ ቤስቲን በተላላነት እንዲያስረክቡት ጥቂት የዋሃን አትዮጵያዊያን ስደተኞችን አይናችሁን ጨፍኑና ላሞኛ ችሁ በሚል ቁጭ በሉ ጮሌነት በአፍዝ አደንዝዝ ዘዬው ይሞጨልፋቸው ገብቷል፡፡

ይህንን እስካሁን ከታዩት የሃሳዊ መሲህ ትወናዎች ወደር ያልተገኘለት የማጭበርበር ዘዴ የግንቦት 7 መሪዎች መካናቸው እምብዛም አይገርምም። ይልቅየስ የሚያስደምመው ራሱን መሳቂያ መሳለቂያ ለማድረግ በተጎነጎነለት የተንኮል ቡልኮ ለመከናነብ ይሁንታውንና ዝግጁነቱን ያለማመንታት የሚገልፀው ምስኪን ኢትዮጵያዊው ስደተኛ ነው። ምነው ቢሉ አንድ ሰው አንዴም ሁለቴም ሊታለል ይችላል ሁሌ የሚታለል ግን ተላላ ሳይሆን የማሰብ አእምሮውን ሌሎች በሪሞት ኮንትሮል እንዲቆጣጠሩለት በፈቃደኝነት አሳልፎ የሰጠ የፖለቲካ የዋህ ፍጡር ብቻና ምን ጊዜም መሬት ላይ ያለውን እውነታን ሳይሆን ምናባዊ ልብ ወለድ ጽንፍ የሚያምን በቀን ቅዥትና በሌሊት የሕልም ዓለም ውስጥ የሚኖር ምስኪን የፖለቲካ ግብዣ ብቻ ነው።

የዓለም የኢኮኖሚ ጠበብትና አንቱ የተሰኙ ዓለም አቀፋዊ ተቋማት ጭምር ኢትዮጵያ ሃገራችን በትክክለኛው የልማት መስመር ላይ የማይቀለበስ ሕገ መንግሥታዊና ፌዴራላዊ ሥርዓት ጎዳና ላይ እየጨመረ እየጎለበተ በሚሄድ የዲሞክራሲያዊ ባህል ንብብርሽ ሂደት ላይና በሰላም ጎዳና ላይ ተሰማርታ እየተጓዘች ያለች ለመሆኗ ከሚሰጡት ምስካሬም በላይ በተጨባጭ የሕዝቡ ኑሮ ቀስ በቀስ ደረጃ በደረጃ እየተሻሻለ ለመሆኑ በጎ ማሳያዎች በሚዳሰሱበትና በሚጨበጡበት በአሁኑ ወቅት የግንቦት 7 የባህር ማዶ ንቅናቄ የሽብርተኝነት ናፋቂነትና የጦር ሰባቂነት ጩኸት የኢትዮጵያን ሰላም ልማትና ዕድገት የሕዝቦችዋን ፍትህ፣ ሰብአዊ መብትና መልካም አስተዳደርን ተቋድሰው ወደ ላቀ የኑሮ ደረጃ ሲሸጋገሩ ላለማየት በደንቃራነት ከተሰለፉ ደመኛ ጠላቶች መሣሪያ ከመሆን ውጭ ሌላ ፍቺ ከቶ ሊሰጠው አይችልም።

የግንቦት 7 መሪዎች በቅድሚያ በሰላማዊ ውድድር እናምናለን ሲሉ ቀላል የማይባል የፓርላማ መቀመጫ በፌዴራል ፓርላማና በአንዳንድ ክልሎች ሲያገኙ የኢትዮጵያ ሕዝብ የዘረጋላቸውን የሰላም ምንጣፍ ረግጠው ድብቅ ዓላማቸውን በአደባባይ ነውጥና ሽብር ሊያሳኩ ሲንቀሳቀሱ ዓይናችሁን ላፈር ብሎ በሕግ ቁጥጥር ሥር ካዋላቸው በኋላ "ማሪኝ አገሬ" በማለት በሕዝብና በመንግሥት እግር ወድቀው የለመኑት ይቅርታ ሲሰጣቸው ዳግም የኢትዮጵያን ሕዝብ ይቅርታ ረግጠው ይኸውና አሁን ደግሞ የፈሪ ሳንጃቸውን ከኒውዮርክና ከሎንዶን ሰገነታቸው ወድረውበታል።

የሰሞኑ የግንቦት 7 ንቅናቄ ለያዥ ለገራዥ በሚያስቸግር መልኩ እዩኝ እዩኝ ብሎ የመውረግረግ ድራማ የሚፈነጥቀው ማሳያ ደግሞ የአማራ ሕዝብ ጠበቃ ሆኖ ብቅ በማለት የተከናነበው ካባ ነው። የአዛኝ ቅቤ አንጓች እንዲሉ አበው እንዲህ ያለውን ዓይኑን በጨው ያጠበውን ፈጣጣ ክስተት ሲያጋጥማቸው፤

የአማራው ሕዝብ እኮ በደሙ እየዋጀ በከፈለው መስዋዕትነት በብአዴን መሪነት የተጋረጡበትን ፈታኝ ሁኔታዎች በድል አድራጊነት እየተወጣ ለዛሬው የትግል ፍሬ የበቃ ወደር የማይገኝለት ታጋይ ሕዝብ ነው። የዛሬዎቹ የግንቦት 7 ንቅናቄ መሪዎች እኮ ትላንት ብአዴን አይቀሬውን የተጋድሎ ታሪክ በደሙ እየጻፈና እያቀለመ ወደ ወሳኝ ና አሁን ወደ ሚገኝበት ከቶውኑ ወደ ማይቀለበሰው የትግል ምዕራፍ የሰላምና የዲሞክራሲ ቀንዲል ሲገሰግስ ከአንድም ሁለቴም ወገቤን በማለት ሸብረክ ብለው ቀኝ ኋላ ዙር ያሉ ለመሆናቸው ሕያው የአደባባይ ምስጢር ነው። እናም አሁን እዩኝ እዩኝ ማለት በኋላ ደብቁኝ ደብቁኝ ለማለት አያመችም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ቀላልና ግልጽ ነው። ማንኛውም የሕዝብንና የሃገርን ጥቅም አስቀድማለሁ የሚል ድርጅትና ግለሰብ የሕዝቡን የልብ ትርታ አዳምጦ ከሱ ጋር የሚጣጣም፣ የሚዋሃድ፣ የሚናበብና በእርሱም ጊዜያዊና የዘለቄታ ፍላጎት አኳያ የተቃኘ የነቢብና የገቢር ራዕይ ካላቀረበ ሕዝብ አክ እንትፍ ብሎ እንደሚሸኘው ከታሪክ የምንማረው እውነታ ብቻ ሳይሆን የዛሬው የኢትዮጵያ ሕዝብ የዕለት ተዕለት ሕያውና ጠጣር ሃቅ ነው። የሕዝብ ፍላጎት ሰላም፣ ልማትና ዲሞክራሲ ሆኖ እነኝህም ሊረጋገጡ የሚችሉት በሕጋዊነትና በሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ማዕቀፍ ሥር በተንደረከኩ ሰላማዊ፣ ፓርላሜንታዊና ዲሞክራሲያዊ ሂደታዊ ፋክክር ብቻ ነው።

የግንቦት ሰባት ምርጫ ጦርነት፣ ሽብር፣ ነውጥ፣ ቀውስ፣ ጀብደኝነት፣ ሥርዓተ አልበኝነትና ትርምስ ስለሆነ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ምርጫ ጋር ፊት ለፊት የሚላተም ፍየል ወዲህ ቅዝምዝም ወዲያ እንዲሉ በዲሞክራሲያዊነት ዳባ ሥር የሽብርተኝነት ደባ ነው።